# የኢትዮጵያ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት ተቋማት ጥምረት ለጥራት

# Ethiopian Primary Health Care Alliance for Quality (EPAQ)

## የአተገባበር መመርያ

FDRE Ministry of Health

# የኢትዮጵያ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት ተቋማት ጥምረት ለጥራት

# Ethiopian Primary Health Care Alliance for Quality (EPAQ)

የአተገባበር መመርያ

ሰኔ 2009 ዓ.ም

ጤና ጥበቃ ሚኒሰቴር

# ማውጫ


ትርጉም ....... vi

1. መግቢያ ....... 1

2. ዓላማ ....... 2

3. ኢላማ የተደረጉ የጤና ተቋማት ....... 2

4. ከኢትዮጵያ ሆስፒታሎች ጥምረት ለጥራት (EHAQ) ጋር ያለው ትስስር ....... 2

5. የመጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት ተቋማት ጥምረት ለጥራት (EPAQ) አሰራር ....... 3

5.1. የመጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት ተቋማት ጥምረት ለጥራት (EPAQ) ብሄራዊ ክላስተር/ትስስር ....... 3

5.2. የመጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት ተቋማት ጥምረት ለጥራት (EPAQ) ሞዴል ክላስተሮች/ትስስር ....... 4

6. የመጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት ተቋማት ጥምረት ለጥራት (EPAQ) መስፈረቶች ....... 4

6.1. የኢትዮጵያ የጤና ጣቢያ አገልግሎት ሪፎርም የአፈፃፀም መመሪያ (EHCRIG) ....... 4

6.2. የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሃዶች ቁልፍ የዉጤት መለኪያዎች (KPIs) ....... 5

6.3. የወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት ሥራ አመራር መለኪያ ....... 5

6.4. የለዉጥ ፓኬጆች ....... 5

7. የመጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት ተቋማት ጥምረት ለጥራት (EPAQ) ዝርዝር ተግባራት ....... 6

7.1. የስራ አፈፃፀም ግምገማ ....... 6

7.2. የስራ ምልከታ ....... 6

7.3. የለዉጥ ፓኬጆች/ ፅንሰ ሃሳቦች ....... 7

8. የባለድርሻ አካላት ሚና ....... 7

8.1. ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ....... 7

8.2. ጤና ጥበቃ ቢሮዎች/ከተማ አስተዳደሮች ....... 8

8.3. የዞን ጤና መምሪያዎች ወይም ክፍለ ከተሞች ....... 9

8.4. የወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤቶች ....... 9

8.5. የመሪ ጤና ጣቢያ ኃላፊነት እና የስራ ድርሻ ....... 10

8.6. የአባል መጀመሪያ ጤና ክብካቤ አሀድ ኃላፊነት እና የስራ ድርሻ ....... 10

8.7. ሆስፒታሎች ....... 11

8.8. የአጋር ድርጅቶች ሃላፊነት እና የስራ ድርሻ ....... 11

9. የበጀት ምንጭ እና አጠቃቀም ....... 12

10. ክትትልና ግምገማ ....... 12

## መቅድም

ኢትዮጵያ እየተከተለች ያለውን መከላከልን መሰረት ያደረገ የጤና ፖሊሲ የተገኙትን ድሎች ለማስቀጠል መንግስት ሁለተኛውን የሀገራችን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አካል የሆነውን የጤናው ዘርፍ የትራንስፎርሜሽን ዕቅድን ተግባር ላይ በማዋል ፍትሃዊነትን፣ መሠረታዊ የጤና አገልግሎት ሽፋንና አጠቃቀምን፣ የጤና ክብካቤ ጥራትንና በሁሉም ደረጃ የመፈፀም አቅምን ለማሻሻል እየሰራ ይገኛል፡፡ይህን እቅድ በላቀ ደረጃ ለማስፈፀም አራት የትራንስፎርሜሽን አጀንዳዎች ተቀርፀዋል፡፡

እነዚህም፤1. የወረዳትራንስፎርሜሽን 2. የጤና አገልግሎት ጥራት እና ፍትሃዊነት ማረጋገጥ 3. የመረጃ አብዮት መፍጠር እና 4. ተንከባካቢ፤አክባሪ እና ርህሩህ የጤና ባለሙያዎችን ማፍራት ናቸው፡፡ እነዚህን የጤናው ዘርፍ የትራንስፎረሜሽን አጀንዳዎች ለማሳካት የፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ከክልል ጤና ቢሮዎች ጋር በመተባበር የአፈጻጸም ስልቶችን እና አጋዥ መመርያዎችን በማውጣት በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡ ይህም የኢትዮጵያ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት ተቋማት ጥምረት ለጥራት (Ethiopian Primary Health Care Alliance for Quality (EPAQ) የዚሁ ጥረት አካል ነው፡፡ የጥምረቱ ዋና አላማ በወረዳ ደረጃ በወረዳ ጤና ጽ/ቤት አስተባባሪነት በየሩብ አመቱ የወረዳ ጤና ጽ/ቤት እና በስሩ ያሉት ጤና ተቋማት አፈጻጸም የሚለካበት፤ የልምድ ልውውጥ የሚደረግበት፤ እንዲሁም መረጃን መሰረት ያደረገ የውሳኔ አሰጣጥ ልምድ የሚዳብርበት አሰራር ስርአት መፍጠር ነው፡፡ በተጨማሪም የተሻለ አፈጻጸም ያላቸውን ጤና ተቋማትን፤ ወረዳዎችን፤ ዞን ጤና መምርያዎችን እና የክልል ጤና ቢሮዎችን ወጥ በሆኑ መሰፈርቶች እውቅና ለመስጠት ያግዛል፡፡

ይህ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት ተቋማት ጥምረት ለጥራት(EPAQ) አሰራር በወረዳዎች ሲከናወን የነበረውን የሩብ አመት የመጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት ተቋማት ግምገማ ወጥ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲከናወን ያደርጋል፡፡ ስለሆነም ሁሉም ክልል ጤና ቢሮዎች፤ የዞን ጤና መምርያዎቸ፤ የወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤቶች እና የጤና ተቋማት በዚህ የጤና ዘርፍ ትራንስፎርሽን አጋዥ መመርያ ሁለነተናዊ አፈጻጸም ላይ የራሳቸውን ድርሻ እንዲወጡ አሳስባለሁ፡፡

ፕ/ር ይፍሩ ብርሃን (ሚኒስትር)<br>
በኢትዩጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ<br>
የጤና ጥበቃ ሚንስቴር

የኢትዮጵያ ጤና ፖሊሲ ዋነኛ አቅጣጫዎች ከሆኑት መካከል የጤና አገልግሎት አሰጣጡን ተደራሽነት ማረጋገጥና የሚሰጠዉንም አገልግሎት ጥራቱን በጠበቀ መልኩ የህብረተሰቡን የጤና ችግሮችን የመቅረፍ ስትራቴጂዎች ያነገበ መሆኑ በዋነኝነት ይጠቀሳል፡፡ ስለሆነም እንደ ሴክተር መስሪያ ቤት የፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በሃገሪቱ ዉስጥ ጥራቱን የጠበቀና ለህብረተሰቡ ተደራሽ የሆነ የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ስርአት ከመዘርጋት አንፃርና አገልግሎቱም ህብረተሰቡን መሰረት ያደረገ እንዲሆን የተለያዩ ስትራቴጂዎች በመንደፍ በመተግበር ላይ ይገኛል፡፡

በመሆኑም የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ስርአቱ በየተቋማቱ ደረጃዉን የጠበቀ እንዲሆንና የጤና ጣቢያዉ የስራ ፍሰትና አመራር ስርአቱን በጠበቀ ሁኔታ በሁሉም ጤና ጣቢያዎች ደረጃዉን የጠበቀ ከማድረግ አንጻር በፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የጤና ጣቢያ ሪፎርም ትግበራ መመሪያ ሰነድ በማዘጋጀት ከየክልል ጤና ቢሮዎችና በየደረጃዉ ከሚገኙ የዞንና የወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤቶች ጋር በመሆን በጤና ጣቢያዎች ለመተግበር ጥረት የማድረግና በአተገባበሩ ሂደት ላይ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ይሁን እንጂ ሪፎርሙን ከማስፈፀም አንፃር ሁሉም የኢትዮጵያ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት ተቋማት በተመሳሳይ ፍጥነት እና ጥራት ሪፎርሙን ተግባራዊ እንዲያደርጉ እና ጥራትን ከማሻሻል አንጻር የተለያዩ ጥሩ ተሞክሮዎች በተለያዩ ቦታ መገኘታቸው የመጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት ተቋማት በአንድነት የሚሰሩበት እና ልምዳችውን የሚለዋወጡበት አሰራር እንደሚያስፈልግ ታምኖበታል፡፡ በመሆኑም የኢትዮጵያ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት ተቋማት ተሞክሮዎቻቸውን እንዲለዋወጡ እና በጋራ ለጥራት እንዲንቀሳቀሱ ይረዳ ዘንድ የኢትዮጵያ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት ተቋማት ጥምረት ለጥራት (Ethiopian Primary Health Care Alliance for Quality (EPAQ) ተመስርቷል፡፡ የዚህን ጥምረት አሰራር፣በውስጡ የሚሳተፉትን ባለድርሻ አካላትን ሃላፊነት እና የስራ ድርሻቸውን ለማስጨበጥ እና መሰረታዊ አካሄዱን ለማሳወቅ ሲባል ይህ ማንዋል አስፈላጊነቱ ታምኖበት ተዘጋጅቷል፡፡
ስለዚህም በዚህ ማንዋል መሰረት ሁሉም አጋር ድርጅቶች ጥምረቱን በማቀድ፣ በማስፈጸም፣በመከታተል እና በመገምገም በተቀመጠላቸው ሀላፊነት እና የስራ ድርሻ መሰረት ከተንቀሳቀሱ የጥምረቱን አላማ ለማሳካት አብይ ድርሻ እንደሚኖረው የሚኒስተር መስሪያ ቤቱ እምነት ነው፡፡

ዶ/ር ደሳለኝ ጥጋቡ (ዳይሬክተር)
የክሊኒካል አገልግሎቶች ዳይሬክቶሬት

## ምስጋና

የፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በዚህ የኢትዮጵያ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት ተቋማት ጥምረት ለጥራት (Ethiopian Primary Health Care Alliance for Quality (EPAQ) ዝግጅት ላይ የተሳተፉ ባለሙያዎችንና ድርጅቶችን በክሊኒካል አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ባለሙያዎችና በተለያዩ ጊዜያት የመመሪያዉን ይዘት ለማዳበር ከፍተኛ ድጋፍ ላደረጉ አጋር አካላትን ማመስገን ይፈልጋል፡፡ መመሪያዉ በዚህ ሁኔታ እንዲዳብርና እንዲዘጋጅ አስተዋጽኦ ላደረጉ ለዶ/ር ደሳለኝ ጥጋቡ፤ ለዶ/ር ይበልጣል መኮንን፤ ለወ/ሪት ሜላት መንበሩ፤ለአቶ አብርሃም ዘርይሁን እና ለዶ/ር ነጻነት ፈጠነ ልባዊ ምስጋና ያቀርባል፡፡

# ትርጉም

1. **የኢትዮጵያ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት ተቋማት ጥምረት ለጥራት** Ethiopian Primary Health Care Alliance for Quality (EPAQ) - ከፍተኛ አፈፃፀም ያላቸዉ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሃዶችን (ጤና ጣቢያዎችና ጤና ኬላዎችን)መፍጠር ዓላማ ያደረገና የመጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት ተቋማት በወረዳ ደረጃ ጥምረትን በመፍጠር መረጃ የሚለዋወጡበት እና በጋራ የሚሰሩበት አሰራር ነዉ
2. **የለውጥ ፓኬጅ**-በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና በክልሎች የሚመረጥ እና ለተወሰነ ጊዜ ጥምረቱ እንዲያተኩርበት የሚደረግ የአገልግሎት አይነት ሲሆን በዚህ በተመረጠ የአገልግሎት አይነት ላይ በመመስረት መሪ እና አባል የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሀዶች ይመረጣሉ፣ ጥሩ ተሞክሮዎችም ይቀመራሉ
3. **መሪ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሀድ** (Lead PHCU) - በተመረጠው የትኩረት አገልግሎት ላይ ጥሩ አፈፃፀም ያሳየ የመጀመሪያ ጤና ክብካቤ አሀድ( ጤና ጣቢያ እና በስሩ ያሉ ጤና ኬላዎች) ሲሆን በ ወረዳ ጤና ጽ/ቤቶች ክትትል፤ በመረጃዎች እና በጉብኝት ውጤቶች በመመስረት የሚመረጥ ይሆናል
4. **አባል የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሀድ**- ከመሪው የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሀድ በትኩረት አገልግሎቱ ላይ ልምድ እንዲቀስም በመሪው ስር የታቀፉ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሀዶች ናቸዉ
5. **እጅብታ** (Cluster) - በአንድ ወረዳ ስር የሚገኙ አንድ መሪ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሀድ( ጤና ጣቢያ እና ጤና ኬላዎች) እና በስሩ የታቀፉ አባል የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሀዶችን የሚይዝ ሲሆን በተመረጠው የትኩረት አገልግሎት ላይ እርስ በእርስ ተሞክሮዎችን ይለዋወጣሉ ያሳዩትንም ለውጥ ይገመግማሉ
6. **የወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት ሥራ አመራር መለኪያ**:የወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት ሥራ አመራርን መስፈርትን በመጠቀም የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሃዶችን አፈፃፀም ለማሻሻል የሚያደርገዉን ጥረትና የወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤቱን የአመራር አቅም ሚዛናዊ በሆነ መልክ ለመለካት የሚጠቅም መለኪያ ነው፡፡
7. **የሆስፒታሎች ጥምረት ለጥራት** - (Ethiopian Hospital alliance for Quality) የሆስፒታል ኢንዱስትሪው ከራሱ መልካም ተሞክሮ በመማር በተደራጀ መልኩ ፈጣን እና ቀጣይነት ያለው የህክምና አገልግሎት ጥራት መሻሻልን ለማምጣት ያለመ አሰራር ነው

## 1. መግቢያ

በጤና ተቋማት መካከል ጥምረትን በመፍጠር፣የመረጃ ልዉዉጥንና መማማርን በማመቻቸት የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራትን ለማሻሻል የጤና ተቋማት ጥምረት መፍጠር ከዚህ ቀደም ተግባር ላይ የዋለ አሰራር ነው፡፡በሀገራችን ውጤታማነቱ የተረጋገጠው  የኢትዮጵያ ሆስፒታሎች ጥምረት ለጥራት (EHAQ) አንዱ ማሳያ ነዉ፡፡

እ.ኤ.አ በ2012 የተጀመረዉ የኢትዮጵያ ሆስፒታሎች ጥምረት ለጥራት /Ethiopian Hospitals Alliance for Quality/(EHAQ) በኢትዮጵያ ሆስፒታሎች የታካሚዎች አገልግሎት የመጠቀም ደረጃን በከፍተኛ ደረጃ ጨምሯል፡፡ የኢትዮጵያ ሆስፒታሎች ጥምረት ለጥራት የአቻ ሆስፒታሎች የጋራ መማማርን ለማመቻቸት፣ የብሄራዊና የእጅብታ(ክላስተር) ስብሰባዎችን ለማካሄድ፣ ለሙያዊ ድጋፍ የመሪ ሆስፒታሎች ጉብኝትና በለዉጡ የሚካተቱ የጥራት ማሻሻያዎች ላይ የሚደረግን ጥረት ለመምራት የተደራጀ አሰራር ነዉ፡፡ የኢትዮጵያ ሆስፒታሎች ጥምረት ለጥራት  በፌደራል ጤና ጥበቃና ክልል ጤና ጥበቃ ቢሮዎች ጠንካራ ባለቤትነት ቀጣይነት ያለው ሊስፋፋ የሚችልና ሁሉን አሳታፊ የጥራት ማሻሻያ አሰራር  መሆኑን ያስመሰከረ ነዉ፡፡

የፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ከኢትዮጵያ ሆስፒታሎች ጥምረት ለጥራት አሰራር ትምህርት በመዉሰድ ከፍተኛ አፈፃፀም ያላቸዉ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሃዶችን (ጤና ጣቢያዎችና ጤና ኬላዎች)መፍጠር ዓላማ ያደረገና ከጤናዉ ዘርፍ የትራነስፎርሜሽን ዕቅድ አጀንዳዎችና ከወረዳ ትራንስፎረሜሽን ጋር የሚያያዝ ተመሳሳይ አሰራር በአገር አቀፍ ደረጃ  የኢትዮጵያ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት ተቋማት  ጥምረት ለጥራት/Ethiopian Primary Health Care Alliance for Quality (EPAQ) ለመተግበር አቅዷል፡፡ይህ ጥምረት፣ ጥራትን ለማሻሻል የትብብር ክላስተሮችን በመፍጠር ከኢትዮጵያ ሆስፒታሎች ጥምረት ለጥራት (EHAQ) ሞዴል ጋር የሚመሳሰል ሲሆን በአገሪቱ የሚገኙ ከ3547 ያላነሱ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት ተቋማት  (ጤና ጣቢያ እና ጤና ኬላዎች) እና ሁሉንም የወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤቶችን ለማቀፍ ያለመ አሰራር ነዉ፡፡ጥምረቱ በመሰረታዊ ጤና አገልግሎት ተቋማት  አገልግሎት አሰጣጥ ጥራት ላይ ከፍተኛ ለውጥ  ያመጣል ተብሎ ይጠበቃል፡፡  ከዚህም በተጨማሪ የወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት የዚህ የጥምረት አሰራር ዋና አካል በመሆን በወረዳዉ ዉስጥ የሚገኙትን የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ተቋማት ንና ሌሎች ባለድርሻ አካላትን  በማቀናጀት፣ በማስተባበር፣ በመደገፍና በማስተዳደር ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡ ይህ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት ተቋማት ጥምረት ለጥራት አሰራር በወረዳዎች ሲከናወን የነበረውን የሩብ አመት የመጀመሪያ ደረጃ ጤና

አገልግሎት ተቋማትን ግምገማ በመተካት ግምገማው ወጥ እና ውጤታማ እንዲሆን ያደረጋል፡፡ ይህ ሰነድ የኢትዮጵያ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት ተቋማት ጥምረት ለጥራትን (EPAQ) በሀገር ዓቀፍ ደረጃ ለመተግበር የተዘጋጀ መመርያ ነዉ፡፡

## 2. ዓላማ

የኢትዮጵያ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት ተቋማት ጥምረት ለጥራት (EPAQ) ዓላማው በመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሃድና ወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት የአገልግሎት ጥራትና ሽፋን ለማሻሻል፣ በጋራ መማማርን ለማጎልበት፤ እንዲሁም ከፍተኛ አፈፃፀም ለአላቸዉ ወረዳዎችና የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሃዶች ዕዉቅና ለመስጠት ነዉ፡፡

## 3. ኢላማ የተደረጉ የጤና ተቋማት

የኢትዮጵያ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት ተቋማት ጥምረት ለጥራት (EPAQ) በዋናነት ኢላማ የሚያደርገው የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሃድና የወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት የአመራር ስርዓት ላይ ነዉ፡፡ የትብብር ክላስተሮች የሚመሰረቱት በወረዳዉ ዉስጥ በሚገኙት የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሃዶች ሲሆን በተመሳሳይም በዞኑ ዉስጥ የሚገኙት ወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤቶችም በክላስትር እንዲተሳሰሩ በማድረግ መማማርን የማመቻቸት፤ አፈፃፀማቸዉን በማወዳደርና ከፍተኛ ክንዉን ያላቸዉን በመለየት ዕዉቅና መስጠትን ይጨምራል፡፡

## 4. ከኢትዮጵያ ሆስፒታሎች ጥምረት ለጥራት (EHAQ) ጋር ያለው ትስስር

የመጀመሪያ ደረጃና ጠቅላላ ሆስፒታሎች ለኢትዮጵያ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት ተቋማት ጥምረት ለጥራት (EPAQ) መሳካት ከፍተኛ ሚና ይኖራቸዋል፡፡ በኢትዮጵያ ሆስፒታሎች ጥምረት ለጥራት (EHAQ) መዋቅር አማካኝነት የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሃዶችን በክሊኒካል ሜንተሪንግ፣ በታካሚ ቅብብሎሽና ሪፎርም አፈፃፀም ስራዎች በመደገፍና ማብቃት ትልቅ ሚና ይጫወታሉ፡፡

የሆስፒታሎቹ አንዱ ዓላማ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት ተቋማት ጥምረት ለጥራትን (EPAQ) መደገፍ ነው፡፡ በዚህ መሰረት አንድ ሆስፒታል በስሩ ያሉትን ሁለት EPAQ ክላስተሮችን የሚመሩ መሪ ጤና ጣቢያዎችን የአሰራር ሂደት ሆስፒታሎቹ በሚያዘጋጁት የሆስፒታል የክስተር ስብሰባዎች ላይ በመገኘት ይገመግማሉ፡፡ በተጨማሪም የመሪ ጤና ጣቢያዎች እና የአባል ጤና ጣቢያዎች ትስስር እና የመደጋገፍ ሂደት በመገምገም አቅጣጫዎችን

ያስቀምጣል፡፡የጤና ጣቢያ እና የሆስፒታሉ ሪፎርም አፈጻጸም፤የቁልፍ ዉጤት መለኪያዎች አፈጻጸም፤ የወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት ሥራ አመራር መለኪያ እና የለዉጥ ፓኬጆች አፈጻጸም እንደትኩረት አጀንዳ ተወስደው ክትትል ይደረግባቸዋል፡፡

## 5. የመጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት ተቋማት ጥምረት ለጥራት (EPAQ) አሰራር

### 5.1. የመጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት ተቋማት ጥምረት ለጥራት (EPAQ) ብሄራዊ ክላስተር/ትስስር

የመጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት ተቋማት ጥምረት ለጥራት (EPAQ) አሰራር ዋና ዓላማዉ በአገሪቱ በሁሉም ወረዳዎች የትብብር ክላስተሮችን/እጅብታዎችን መመስረት ነዉ፡፡ እያንዳንዱ ክላስተር ሁሉንም በወረዳዉ ዉስጥ የሚገኙትን የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሃዶችን የሚያካትት ሲሆን ለሌሎች አርአያ/መሪ መነሻ የሚሆን አንድ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሃድ ይኖራል፡፡ ስለሆነም፣ይህ የትብብር ክላስተር በወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት አስተባባሪነት ይመራል፡፡ በእያንዳንዱ ወረዳ የጥምረቱ መለኪያዎች መስፈርት መሰረት የመጀመሪያ ዙር መሪ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሃድ ይመረጣል (ቀጣይ ክፍሎችን ይመልከቱ)፡፡በዓመታዊ የውጤት ምዘና መሰረት የክላስተሩ መሪ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሃድ ለዉጥ መረጣ/ክለሳ ይካሄዳል፡፡ እንደ ክልሉ፣ ዞኑ ወይንም የከተማ አስተዳደሩ ነባራዊ ሁኔታ፤ የክልል ጤና ጥበቃ ቢሮዎች በወረዳዎች መካከል የእርስ በእርስ መማማር መድረኮችን ያመቻቻሉ፡፡ እንዲሁም ከፍተኛ አፈፃፀም ላላቸዉ ወረዳዎችም ዕዉቅና ይሰጣሉ፡፡

የመጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት ተቋማት ጥምረት ለጥራት (EPAQ) የትብብር ክላስተር አባላት ስብጥር እንደሚከተለዉ ይሆናል፤ የወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት ኃላፊና ምክትል ኃላፊ፣ በወረዳዉ ዉስጥ ካሉት ከእያንዳንዱ ጤና ጣቢያ ሁለት ተወካይ(የጤና ጣቢያ ዳይሬክቴር እና ተወካይ) እና ከየጤና ጣቢያ የስራ አመራር ቦርድ አንድ ተወካይ ይሆናል፡፡ ስለሆነም በአንድ ወረዳ ዉስጥ በአማካይ ከ5-10 ጤና ጣቢያዎች ቢኖሩ፣ በክላስተሩ ከ20-25 አባላት ይኖራሉ ማለት ነው፡፡ በጤና ጥበቃ ቢሮዎችም የመጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት ተቋማት ጥምረት ለጥራት (EPAQ) ክላስተርን እስከ 2009 ዓ.ም መጨረሻ በሁሉም ወረዳዎች በመመስረት ወደ ስራ እንዲገቡ ይደረጋል፡፡

### 5.2. የመጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት ተቋማት ጥምረት ለጥራት (EPAQ) ሞዴል ክላስተሮች/ትስስር

የፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ከክልል ጤና ጥበቃ ቢሮዎች ጋር ሞዴል የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሃዶችን በመጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት ተቋማት ጥምረት ለጥራት (EPAQ) አሰራር ለመለየት ይሰራል። ሞዴል ጣቢያዎችን መፍጠር ወደ ሌሎች ጥምረቶች ሊሰፉ የሚችሉ ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመርና በማስፋፋት ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል። አንድ ሞዴል የመጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት ተቋማት ጥምረት ለጥራት (EPAQ) ወረዳ/ክላስተርና መሪ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሃድ በእያንዳንዱ ዞን በሁሉም ክልሎች ይመረጣል። በድምሩ 80 የመጀመርያ ደረጃ ጤና አገልግሎት ተቋማት ጥምረት ለጥራት (EPAQ) ሞዴል የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሃድ (አንድ በእያንዳንዱ ዞን) ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ ከክልል ጤና ጥበቃ ቢሮና በአካባቢዉ ከሚሰሩ አጋር አካላት የቅርብ ክትትልና ሙያዊ ድጋፍ ያገኛሉ።

ሞዴል የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሃዶች የተጠናከረ ሙያዊ ድጋፍ በሜንተሪንግና በድጋፋዊ ጉብኝት መልኩ በቦታዉ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ ከክልል ጤና ጥበቃ ቢሮና አጋር አካላት ያገኛል።

## 6. የመጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት ተቋማት ጥምረት ለጥራት (EPAQ) መስፈረቶች

የኢትዮጵያ መጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት ተቋማት ጥምረት ለጥራት (EPAQ) በመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሃዶችና በተመረጡ መሪ የመጀመሪያ ጤና ክብካቤ አሃዶች የትብብር የአፈፃፀም ማሻሻያዉን ለመምራትና ለመለካት የሚከተሉትን ቁልፍ መስፈርት እና ጠቋሚዎች ይጠቀማል።

### 6.1. የኢትዮጵያ የጤና ጣቢያ አገልግሎት ሪፎርም የአፈፃፀም መመሪያ (EHCRIG)

የኢትዮጵያ የጤና ጣቢያ አገልግሎት ሪፎርም አፈፃፀምመመሪያ (EHCRIG) የተለያዩ መስፈርቶች ያሉትና የጤና ጣቢያዎችን አሰራር ለማሻሻል በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ተዘጋጅቶ ስራ ላይ ውሏል። የኢትዮጵያ የጤና ጣቢያ አገልግሎት ሪፎርም የአፈፃፀም መመሪያ የጤና ጣበያዎችን አፈፃፀም ለማሻሻል ዋና መግባቢያ ሆኖ ያገለግላል። የኢትዮጵያ መጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት ተቋማት ጥምረት ለጥራትም ሪፎረሙን ለማሳደግ በአገሪቱ ባሉት ሁሉም ጤና ጣቢያዎች እንደ ማሳለጫ መሳሪያ ሆኖ ያገልግላል።መሪ ጤና ጣቢያዎችም በጥቅል የሪፎረም አፈፃፀምና ጥሩ ተሞክሮዎችን በክላስተሮቻቸዉ ዉስጥ እንዲተገብሩና እንዲያሰፉ ይጠበቃል።

## 6.2. የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሃዶች ቁልፍ የዉጤት መለኪያዎች (KPIs)

የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ለመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሃዶች መረጃን መሰረት ያደረገ አፈፃፀምን ለማሻሻል የሚረዱ ቁልፍ የውጤት መለኪያዎችን ለይቷል፡፡ጤና ጥበቃ ቢሮዎች እንደ ክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ተጨማሪ ቁልፍ የአፈፃፀም መለኪያዎችን የመጠቀም አማራጭ አላቸዉ፡፡ በኢትዮጵያ መጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት ተቋማት ጥምረት ለጥራት (EPAQ) አማካኝነት ቁልፍ የአፈፃፀም መለኪያዎች የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሃዶችን የአፈፃፀም ለውጥና ስኬቶችን ለመለካት፣ የተጠያቂነትን ባህል ለማሳደግና መረጃን መሰረት ያደረገ ዉሳኔ ለመስጠት ያገለግላሉ፡፡ መሪ ጤና ጣቢያዎችም ቁልፍ መለኪያዎችንና መረጃን መሰረት ያደረገ ዉሳኔን በማሳለፍ የአፈፃፀም መሻሻል ማሳየት ይጠበቅባቸዋል፡፡

## 6.3. የወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት ሥራ አመራር መለኪያ

የወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት ለመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሰራር በአመራር፣ በአስተዳደር፣ በማስተባበርና በአቅርቦት መሻሻል ኃላፊነቱ ወሳኝ ነዉ፡፡የወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት ሥራ አመራር መስፈርትን መጠቀም የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሃዶችን አፈፃፀም ለማሻሻል የሚያደርገዉን ጥረትና የወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤቱን የአመራር አቅም ሚዛናዊ በሆነ መልክ ለመለካት አስተዋፅኦ አለዉ፡፡ ስለሆነም የወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት ሥራ አመራር መለኪያ የወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤቶችን የአመራር አፈፃፀማቸዉን በቀጣይነት ለመለካት ይጠቅማል፡፡ አሁን ያሉት የወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት የሥራ አመራር ደረጃዎች የተዘጋጁት ለገጠር ወረዳዎች ሲሁን በቀጣይ ለከተሞችና ልዩ ድጋፍ ለሚሹ የክልል ወረዳዎች እንዲስማሙ ሆነዉ ይዘጋጃሉ፡፡

## 6.4. የለዉጥ ፓኬጆች

የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር አግባብነት ያላቸዉን ተደጋጋፊ መሳሪያዎችንና የአፈፃፀም መመሪያዎችን መሻሻል ያለባቸዉን የለዉጥ ፓኬጆች/ሃሳቦች በመለየት ያደራጃል፡፡ በየዓመቱ የተወሰኑና ትኩረት የሚሹ የለዉጥ ሃሳቦች ይለያሉ፡፡እነዚህም የለዉጥ ሃሳቦች መንግስት በያዛቸዉ እንደ ፅዱ፣ምቹና ደህንነቱ የተጠበቀ ጤና ተቋማት መፍጠር፣ሞዴል ቀበሌ መፍጠር፣ የማህበረሰብ ጤና መድንና ሌሎችም ላይ ትኩረት ያደርጋሉ፡፡የለዉጥ ፓኬጆችም በጤና ተቋማት አፈፃፀም ግምገማና እዉቅና አሰጣጥ በማካተት ጥቅም ላይ ይዉላሉ፡፡የተመረጡ የለዉጥ ፓኬጆች በኢትዮጵያ መጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት ተቋማት ጥምረት ለጥራት (EPAQ) የክላስተር አፈፃፀም አንድ የጥራት ማሻሻያ መለኪያ መሳርያ ሆኖ ያገልግላሉ፡፡

## 7. የመጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት ተቋማት ጥምረት ለጥራት (EPAQ) ዝርዝር ተግባራት

የትብብር ክላስተሮች መመማርን ለማመቻቸትና ለጋራ አፈፀም መሻሻል የሚከተሉት ተግባራት ያከናውናሉ ።

### 7.1. የስራ አፈፃፀም ግምገማ

የአፈፃፀም ግምገማ ስብሰባዎች የክላስተሩን የጋራ ክንዉን ለመገምገምና የሩብ ዓመት የልምድ ለዉዉጥ ለማድረግ በክላስተሩ ዉስጥ ያሉ ሁሉም ጤና ጣቢያዎች፣ የክላስተር መሪ ጤና ጣቢያና ወረዳ ጤና ጽ/ቤቱን ጨምሮ ሪፖርት ያቀርባሉ፤ መልካም ተሞክሮዋቸውንና ተግዳሮቶቻቸውን ያካፍላሉ። የሚቀርበዉ ሪፖረት የሚከተሉትን ያካትታል።የኢትዮጵያ የጤና ጣቢያ አገልግሎት ሪፎርም ትግበራ መመሪያ (EHCRIG)፣ቁልፍ መለኪያዎች፣የለዉጥ ፓኬጆች፣ የወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት ሥራ አመራር ስታንዳርድ ይሆናል።ይህን የአፈፃፀም ግምገማ በወረዳዉ እየተካሄደ ካሉ መደበኛ የሩብ አመት ስብሰባዎች ጋር ማቀናጀት ዉጤታማነቱን ለማረጋገጥ ይረዳል። ስብሰባዎቹም የሚታቀዱት፣ የሚደራጁትና የሚመሩት በወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤቱ ይሆናል። የስብሰባ ቦታዉም የስራ ምልከታ በሚካሄድባቸው ጤና ጣቢያዎችን መሰረት ባደረገ ሁኔታ በመቀያየር ይካሄዳል።

**የስራ አፈፃፀም ግምገማ አካሄድ**

- ወረዳ ጤና ጽ/ቤት አሰቀድሞ ሁሉም ጤና ጣቢያዎች ለስብሰባው ዝግጅት እንዲያደረጉ በቂ ግዜ በመሰጠት ያሳውቃል።
- ወረዳ ጤና ጽ/ቤት ከጤና ጣቢያዎች የስራ አፈጻጸም ርፖርት አስቀድሞ በመቀበል አፈጻጸማቸውን ይተነትናል
- ሁሉም ጤና ጣብያዎች የስራ አፈጻጸማቸውን የኢትዮጵያ የጤና ጣቢያ አገልግሎት ሪፎርም ትግበራ መመሪያ (EHCRIG)፣ ቁልፍ መለኪያዎች (ከፒሰ)፣የለዉጥ ፓኬጆች መሰረት በማድረግ ያቅርባሉ ውይይትም ይደረግበታል
- የወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት የወረዳውን ሥራ አመራር መለኪያ እና የጤና ጣቢያዎች የስራ አፈጻጸም ርፖርት በመተንተን በስብሰባው ያቀርባል
- በአገልግሎት ላይ የተገኙትን መልካም ተሞክሮዎችን በሁሉም አባል መጀመሪያ አሀድ ላይ ሊያስፋፉበት የሚችሉበትን መንገድ መቀየስ
- መልካም ተሞክሮዎቹን በማስፋት ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች እና መፍትሄዎቹን ያሰቀምጣሉ

### 7.2. የስራ ምልከታ

የየሩብ ዓመት የስራ ምልከታ የሚደራጁት የኢትዮጵያ መጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት ተቋማት ጥምረት ለጥራት (EPAQ) የትብብር ክላስተሮች ዉስጥ ሁኖ እንደ ድጋፋዊ ጉብኝት ይጠቅማል።ድጋፋዊ ጉብኝቶች በወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቡቱ ስርና አስተባባሪነት በመሪ ጤና ጣቢያዎች የሚደራጁና የሚመሩ ይሆናሉ። ለምልከታ የተመረጠው ተቐም ይጎበኛል፣

ይገመገማል፣ ግብረ መልስም ይሰጠዋል፡፡ ይህም የሩብ ዓመት ድጋፋዊ ጉብኝት ከላይ እንደተጠቀሰዉ የአፈፃፀም ግምገማ ስብሰባ ሂደት ጋር ይቀናጃል፡፡

### 7.3. የለዉጥ ፓኬጆች/ ፅንሰ ሃሳቦች

የጤና ጥበቃ ሚኒስቴርና የክልል ጤና ጥበቃ ቢሮዎች፤ መመሪያዎች፣ አሰራሮችንና የትብብር የጥራት መሻሻያ ጥረቶችን ለመምራት የሚያግዙ በአገሪቱ ከተለያየ አካባቢ የተሰባሰቡ መልካም ተሞክሮዎች የያዙ የለዉጥ ፓኬጆችን/ፅንሰ ሃሳቦችን ያዘጋጃሉ፡፡ የለዉጥ ፓኬጆች ትኩረት የሚያደርጉት በተወሰኑ፣ በተመረጡና በየዓመቱ ሊቀየሩ በሚችሉ ቁልፍ ስራዎች ላይ ይሆናል፡፡ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴርና ጤና ጥበቃ ቢሮዎች በክላስተሩ ዉስጥ ያሉ ጤና ተቋማትን፣ በተለይ በተመረጡ እዉቀታቸዉንና መልካም ተሞክሯቸውን ያካፍላሉ ተብለዉ ለሚጠበቁ መሪ ጤና ጣቢዎች ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣሉ፡፡

## 8. የባለድርሻ አካላት ሚና

በየደረጃዉ አግባብነት ያላቸዉ በፌደራል፣ በክልል፣ በዞንና ወረዳ ደረጃ የሚገኙ ባለድርሻ አካላት የኢትዮጵያ መጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት ተቋማት ጥምረት ለጥራት (EPAQ) ሂደት እንዲተገበር ከፍተኛ ሚና መጫወት ይኖርባቸዋል፡፡

### 8.1. ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር

በፌደራልና በክልል ባለድርሻ አካላት የኢትዮጵያ መጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት ተቋማት ጥምረት ለጥራት (EPAQ) ሞዴልን በይፋ ያስጀምራል፡፡ አፈፃፀሙንም የሚከታተል፣ አግባብነት ያላቸዉ የለዉጥ ሃሰቦችን/ፓኬጆችን የሚቀርፅና ለጤና ጥበቃ ቢሮዎችና የኢትዮጵያ መጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት ተቋማት ጥምረት ለጥራት (EPAQ) ሞዴል ቦታዎች ሙያዊ ድጋፍ የሚሰጥ ብሄራዊ የኢትዮጵያ መጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት ተቋማት ጥምረት ለጥራት (EPAQ) ኮሚቴ ያዋቅራል፡፡ ከፍተኛ አፈፃፀም ላላቸዉ ክልሎች፣ ዞኖችና ወረዳዎች እዉቅና ይሰጣል፡፡

- በዚህ ማንዋል መሠረት ለዚህ ስራ የሚያግዝ አገር አቀፍ አብይ ኮሚቴ (National Steering Committe) ያዋቅራል፡በጥምረቱ ዙሪያ በጋራ ይሰራል
- በየአመቱ የትኩረት አገልግሎት ይመርጣል ለክልሎችም ያስተዋዉቃል
- የመሪ ጤና ጣቢያ መመልመያ መስፈርት ያዘጋጃል ለክልሎችም ለአስተያየት ይልካል
- ከክልሎች ጋር ተቀራርቦ በመስራት በየጊዜው በጥምረቱ ላይ ያለውን ችግር ይለያል በጋራ የመፍትሄ አቅጣጫ ያስቀምጣል
- በመጀመሪያ ምልመላ እና በክልል የተለዩትን ሞዴል ጤና ጣቢያ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት የመሪ ጤና ጣቢያ ሚናን ሊጫወቱ እንደሚችል ያረጋግጣል፡፡

- በየአመቱ በኢትዮጵያ መጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት ተቋማት ጥምረት ለጥራት (EPAQ) መስፈርት መሰረት ጥሩ አፈፃፀም ላሳዩ ክልሎች እዉቅና ይሰጣል
- ለማበረታቻ የሚውል በቂ በጀት ይይዛል
- በሀገር አቀፍ ደረጃ በጥምረቱ እንቅስቃሴ ዙሪያ ከክልሎች ጋር በቅርበት ይሰራል ለዚህም ድጋፍና የክትትል እና ግምገማ ያካሂዳል የመረጃ ሰነድ ያዘጋጃል
- ከክልል ጤና ቢሮዎች ጋር በመሆን ለሞዴል የመጀመሪያ ጤና ክብካቤ አሀዶች እንዲሁም የአገልግሎት ጥራት ማሻሻያ ስራዎች ላይ ሙያዊ እገዛ ያደርጋል
- ከክልል ጤና ቢሮዎች ጋር በመሆን የሞዴል የመጀመሪያ ጤና ክብካቤ አሀዶችን መልካም ተሞክሮ ይቀምራል ለሁሉም ጥምረቶች ያሰራጫል፤አገር አቀፍ የመልካም ተሞክሮዎችን አና የጥሩ ልምድ ልውውጥ መድረክ ያዘጋጃል
- በየአመቱ ጥምረቱ የሚያመጣውን ለውጥ ያጠናል በጥናቱም መሰረት በቀጣዩ ጥምረት ላይ የማሻሻያ ስራ ያካሂዳል

## 8.2. ጤና ጥበቃ ቢሮዎች/ከተማ አስተዳደሮች

የኢትዮጵያ መጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት ተቋማት ጥምረት ለጥራት (EPAQ) አሰራር በመስፋፋት አፈፃፀምን ይከታተላሉ፣

- አግባብነት ያላቸዉ የለዉጥ ፓኬጆችን በመቅረፅ፣ ለወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤቶችና መሪ ጤና ጣቢዎች ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣሉ፣
- በተለያዩ ዞኖች ዉስጥ ባሉት ወረዳዎች መካከል መማማሪያ መድረክን ያመቻቻል
- ከፍተኛ አፈፃፀም ያላቸዉ ዞኖች፣ ወረዳዎችና የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሃዶችን እዉቅና ይሰጣል
- በየዞኑ አንድ ሞዴል የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሃድ በመምረጥ የተለየ ድጋፍ ያደርጋል
- ይህን ስራ የሚከታተል አንድ ባለሙያ ይወክላል፤በክልሉ ያሉትን የፕሮጀክቱ እንቅስቃሴ መረጃ ይይዛል አጠቃላይ የጥምረት ስራውን በዋናነት ይመራል
- በክልሉ በየዞኖቹ ያለውን ጥምረት በቅርበት ይከታተላል ችግሮችም ሲያጋጥሙ የመፍትሄ አቅጣጫ ያስቀምጣል
- ከጤና ጥበቃ ሚንስቴር ጋር በመሆን በክልሉ የሚገኙ ሞዴል መሪ ጤና ጣቢያዎች በመረጡት አና ድክመት በሚታይባቸው የአገልግሎት አይነት ላይ ጠንካራ እገዛ ይሰጣል

ጥሩ ተሞክሮዎችን ይቀምራል በክልሉ ባለው ጥምረት ተሞክሮዎቹ መተግበራቸውን ያረጋግጣል

- በክልሉ የሚገኙ ጥምረቶችን አሰራር በየጊዜው ይገመግማል በክልላዊ የስራ አፈፃፀም ግምገማ ስብሰባ ላይ (Review Meeting) እንደዋነኛ አጀንዳ ይዞ ይገመገማል
- ጥምረቱን ለመከታተል እና ለማገዝ የሚውል በቂ በጀት በየአመቱ ይይዛል
- ከጤና ጥበቃ ሚንስቴር ጋር በመሆን ጥምረቱ ያመጣውን ለውጥ እና የአሰራር ሁኔታን ይገመግማል ለሚቀጥለው ጥምረት የሚሻሻልበትን መንገድ ይጠቁማል።

## 8.3. የዞን ጤና መምሪያዎች ወይም ክፍለ ከተሞች

የኢትዮጵያ መጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት ተቋማት ጥምረት ለጥራት (EPAQ) አሰራርና አፈፃፀምን በቅርበት በመከታተል የተገኙ ተሞክሮዎችን ከሞዴል የጥምረቱ ቦታዎች ወደ ሌሎች ወረዳዎች ያሰራጫሉ። ከፍተኛ አፈፃፀም ላላቸዉ ወረዳዎችና የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሃዶች ዕዉቅና ይሰጣሉ።

- በዞን አንድ ሞዴል የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሃድ በመምረጥ የተለየ ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣሉ።የዞን መዋቅር በሌለባቸዉ ክልሎች የጤና ጥበቃ ቢሮዎች ይህንን ስራ ደርበው ይሰራሉ።
- በስድስት ወር አንድ ጊዜ በዞኑ በሚገኙት ጥምረቶች መካከል የዉይይት መድረክ ያዘጋጃል አፈፃፀማቻን ይገመግማል ለክልል ጤና ቢሮም ጥምረቱን በተመለከተ ሪፖርት ይልካሉ
- የተሻለ አፈፃፀም ላሳዩ ወደዳዎች እዉቅና ይሰጣሉ

## 8.4. የወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤቶች

የወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤቶች የኢትዮጵያ መጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት ተቋማት ጥምረት ለጥራት (EPAQ) የትብብር ክላስተር ያስተባብራሉ።

- ሂደቱንም ሙሉ በሙሉ በባለቤትነት ያስኬዳሉ
- በየዓመቱ መሪ የመጀመሪያ ጤና ክብካቤ አሃዶችን ይመርጣሉ
- በየሩብ አመቱ በተመረጠዉ የጥምረቱ ጤና ተቋም ጉብኝት እና የመወያያ መድረክ ያቅዳሉ፣ያዘጋጃሉ፣ ያስተባብራሉ
- በተመረጠዉ የትኩረት አቅጣጫ የጥምረቱን አፈፃፀም ይገመግማል ፡በጋራ በመሆን የወደፊት አቅጣጫ ያስቀምጣሉ
- የተሻለ አፈጻጸም ላላቸው የመጀመሪያ ጤና ክብካቤ አሀድ እውቅና ይሰጣሉ

- አስፈላጊውን በጀት ይመድባሉ
- መሪ ጤና ጣቢያዎች በሆስፒታል ክለስተር የግምገማ መድረኮች ላይ እንዲሳተፉ ድጋፍ ያደርጋሉ፣ይሳተፋሉ

## 8.5. የመሪ ጤና ጣቢያ ኃላፊነት እና የስራ ድርሻ

- የጥምረቱን ተግባራት ከአባላት ጋር ሆኖ ያቅዳል ያስፈጽማል
- የራሱን ጥሩ ተሞክሮዎች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ለአባል መጀመሪያ ጤና ክብካቤ አሀዶች ያከፍላል ዝቅተኛ አፈጻጸም ያላቸው የአገልግሎት አይነቶች ላይ ከሌሎች ለአባል መጀመሪያ አሀዶች  ተሞክሮ ይወስዳል
- ከተለያዩ መጀመሪያ ጤና ክብካቤ አሀዶች የተቀመሩ ልምዶችን በክልል ጤና ቢሮ ሲቀርብለት እራሱም በመተግበር አባል መጀመሪያ ጤና ክብካቤ አሀዶች ተከታትሎ እንደነባራዊ ሁኔታው ያስተገብራል
- ስለ ስራ አፈጻጸሙ ለመነጋገር በሚዘጋጀው ፎረም ላይ ይገኛል በንቃት ይሳተፋል
- ድክመት ያለበትን የአገልግሎት አይነት ለይቶ ለጤና ጥበቃ ጽ/ቤት እና ለክልል ጤና ቢሮ እገዛ እንዲደረግለት ይጠይቃል
- የጥምረቱን አሰራር እና በትኩረት አገልግሎቱ ላይ ያለውን የራሱን እና የአባል መጀመሪያ ጤና ክብካቤ አሀዶች ለውጥ በየጊዜው ይከታተላል ችግርም ሲኖር ለጋራ ለመፍታት ይጥራል
- የጥምረቱን ስብሰባ ይመራል ቃለ ጉባኤውንም ለዞን እና ክልል ጤና ቢሮ ይልካል
- በጥምረቱ ላይ ችግር በሚከሰትበት ጊዜ ከክልል ጤና ቢሮዎች እና ከዞን ጤና መምሪያ ጋር እንደአስፈላጊነቱ በመነጋገር መፍትሄ ያፈላልጋል
- በየጊዜው የራሱን ለውጥ የተገልጋዮችን እርካታ በትኩረት አገልግሎቱ አንጻር በመለካት እና ህብረተሰቡን በማወያየት ይገመግማል

## 8.6. የአባል መጀመሪያ ጤና ክብካቤ አሀድ  ኃላፊነት እና የስራ ድርሻ

- የጥምረቱን ተግባራት ከመሪ መጀመሪያ ጤና ክብካቤ አሀድ ጋር ሆኖ ያቅዳል
- መሪ መጀመሪያ ጤና ክብካቤ አሀድ  እና ወረዳ ጤና ፅ/ቤት  በሚጠራው የጥምረቱ ስብሰባ ላይ በመገኘት እና በንቁ ሁኔታ ይሳተፋል
- የራሱን ለውጥ ከትኩረት አገልግሎቱ አንፃር ይገመግማል ማነቆዎቹንም በጥምረቱ ስብሰባ ላይ ያቀርባል በጋራ መፍትሄ ያፈላልጋል
- በሌሎች የአገልግሎት አይነቶች ላይ ያለውን ጥሩ ተሞክሮ ለመሪው እና ለሌሎች አባል መጀመሪያ ጤና ክብካቤ አሀድ  ያካፍላል

- ከክልል የሚቀርብለትን የተቀመሩ ጥሩ ተሞክሮዎችን ይፈጽማል እነደነባራዊ ሁኔታ ለውጡንም ይከታተላል
- ባለሞያዎችን መሪው መጀመሪያ ጤና ክብካቤ አሀድ  ድረስ በመውሰድ በትኩረት አገልግሎቱ ላይ ልምድ እንዲወስዱ ያደርጋል
- በየጊዜው የራሱን ለውጥ የተገልጋዮችን እርካታ በትኩረት አገልግሎቱ አንጻር በመለካት እና ህብረተሰቡን በማወያየት ይገመግማል
- የጥሩ ተሞክሮ ቀጣይነት ያለው ትግበራ በቋሚነት ይከታተላል

## 8.7. ሆስፒታሎች

- በክሊኒካልና በታካሚ ቅብብሎሽ ግንኙነት ላይ ለኢትዮጵያ መጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት ተቋማት  ጥምረት ለጥራት (EPAQ) ክላስትሮች በኢትዮጵያ ሆስፒታሎች ጥምረት ለጥራት (EHAQ) መዋቅር አማካኝነት ድጋፍ ይሰጣሉ፡፡

## 8.8. የአጋር ድርጅቶች ሃላፊነት እና የስራ ድርሻ

ሙያዊ፣ የገንዘብና የቁሳቁስ ድጋፋቸዉን ከኢትዮጵያ መጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት ተቋማት ጥምረት ለጥራት (EPAQ) ትግበራ ጋር በማስተሳሰር ለግቡ ስኬታማነት እገዛ ያደርጋሉ፡፡አጋሮች በለዉጥ ፓኬጆች ቀረፃና ስርጭት ላይ በሚሰሩባቸዉ አካባቢም ወረዳዎች ወደ ስራ እንዲገቡና በሚያደርጓቸዉም የክትትልና ግምገማ ጥረቶችና በመሳሰሉት የድጋፍ አስተዋፅኦ ማድረግ አለባቸዉ፡፡

- የፌድራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር አደረጃጀት ውስጥ በሚገኙ አብይ እና ንኡስ ኮሚቴዎች ውስጥ በንቃት ይሳተፋሉ
- በክልል ጤና ቢሮዎች እና በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሞያዊ እገዛቸውን በተፈለገ ጊዜ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣሉ
- እንደ አስፈላጊነቱ በጤና ጥበቃ እና በክልል ጤና ቢሮዎች ጥያቄ መሰረት ለስራው አፈጻጸም የበጀት ድጋፍ ያደርጋሉ
- እንደ አስፈላጊነቱ በጥምረት ስብሰባዎች (Cluster meeting) ላይ በመገኘት ሞያዊ እገዛ ይሰጣሉ

## 9. የበጀት ምንጭ እና አጠቃቀም

የጥምረቱን ቀጣይነት ለማረጋገጥ በዚህ የስራ እንቅስቃሴ ላይ ሁሉም ባለድርሻ አካላት በቂ የበጀት ድጋፍ ሊያደርጉለት ይገባል፡፡ አጋር ድርጅቶች ድጋፋቸውን ማድረግ ይችላሉ፡፡ ከላይ በተጠቀሰው መሰረት እያንዳንዱ ባለ ድርሻ አካላት በአመታዊ የበጀት እቅዳቸው ላይ ለዚህ ስራ ማስፈጸሚያ የሚውል በጀት መመደባቸውን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡ወረዳዎች ለሩብ አመት ግምገማ የመደቡትን በጀት ለዚህ ጥምረቱ ስራ ማከናወኛ መጠቀም ይጠበቅባቸዋል፡፡

በማበረታቻው ፓኬጅ የበጀት ድጋፍ ከመሰጠቱ በፊት ተሸላሚ መጀመሪያ አሀድ በጀቱን ለምን እንደሚያውል ግልጽ የሆነ እቅድ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማዘጋጀት ይኖርበታል፡፡

## 10. ክትትልና ግምገማ

የኢትዮጵያ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት ተቋማት ጥምረት ለጥራት (EPAQ) ሂደት በተለያዩ ደረጃዎች በኢትዮጵያ መጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት ተቋማት ጥምረት ለጥራት (EPAQ)ኮሚቴ ክትትልና ግምገማ ይደረግለታል፡፡ ይህም ከፍተኛ አፈፃፀም ያላቸዉን ክላስተሮች፣ ዞኖችና ክልሎች ለመምረጥ መሠረት ይሆናል፡፡ኮሚቴው በፌደራል፣ በክልል፣ በዞንና በወረዳ ደረጃ ይዋቀራል፡፡ የአፈፃፀም ክትትልና ግምገማ በዋናነት፤ በኢትዮጵያ የጤና ጣቢያ አገልግሎት ሪፎርም ትግበራ መመሪያ (EHCRIG)፣ቁልፍ መለኪያዎች፣የለዉጥ ፓኬጆችና በወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት ሥራ አመራር መለክያ ላይ መሠረት ያደረገ ይሆናል፡፡

የኢትዮጵያ መጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት ተቋማት ጥምረት ለጥራት (EPAQ) ሑደት በመደበኛ አንድ ዓመት የሚወስድ ሲሆን በዚህ ጊዜም አፈፃፀማቸው የላቀ እና ምርጥ የተሻሻሉ ጤና ጣቢያዎች በወረዳ ደረጃ በእየሩብ ዓመቱ፤አፈፃፀማቸው የላቀ እና ምርጥ የተሻሻሉ ወረዳዎች በየግማሽ ዓመቱ፤ አፈፃፀማቸው የላቀ እና ምርጥ የተሻሻሉ ዞኖችም በክልል ደረጃ በዓመት አንድ ጊዜ እዉቅና ይሰጣቸዋል፡፡ በመጨረሻም አፈፃፀማቸው የላቀ እና ምርጥ የተሻሻሉ ክልሎች በየዓመቱ በፌደራል ደረጃ ዕዉቅና ያገኛሉ፡፡

- ምርጥ የተሻሻለ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሃድ Best Improved PHCU (BIP) የሚመረጠዉ በጥራት ማሻሻያ አፈፃፀሙ መሠረት ይሆናል፡፡ በዓመቱ ዉስጥ በአብዛኛዉ ሩብ ዓመታት ምርጥ የተሸሻለ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሃድ ለሚቀጥለዉ ዓመት መሪ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሃድ ሆኖ ይመረጣል፡፡
- ምርጥ የተሻሻሉ ወረዳዎች Best Improved Woredas (BIW) በሚኖራቸዉ ምርጥ የተሻሻሉ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሃዶች መጠንና (BIPs) በአላቸዉ ከፍተኛ የወረዳ ጤና ሥራ አመራር ዉጤት መሠረት ይመረጣሉ፡፡

- ምርጥ የተሻሻሉ ዞኖች Best Improved Zones (BIZ) በሚኖራቸዉ ምርጥ የተሻሻሉ ብልጫ ባለቸዉ ወረዳዎች (BIWs) መጠን መሠረት ይመረጣሉ፡፡

- ምርጥ የተሻሻሉ ክልሎች Best Improved Region (BIR) በሚኖራቸዉ ምርጥ የተሻሻሉ ብልጫ ባለቸዉ ወረዳዎች (BIWs) መጠን መሠረት ይመረጣሉ፡፡

| ምርጥ የተሻሻሉ ክልሎች(BIR) | ምርጥ የተሻሻሉ ዞኖች(BIZ) | ምርጥ የተሻሻሉ ወረዳዎች(BIW) | ምርጥ የተሸሻለ ጤና ክብካቤ አሃድ(BIP) |
|---|---|---|---|
| • በፌደራል ደረጃ<br>• በየዓመት | • በክልል ደረጃ<br>• በየዓመት | • በዞን ደረጃ<br>• በየግማሽ ዓመት | • በወረዳ ደረጃ<br>• በየሩብ ኣመት |